# ሄፐታይቲስ B ቢኖርብዎት እና ነፍሰ ጡር ቢሆኑ የልጅዎን የእርስዎን ጤንነት እንዴት ይጠብቃሉ



ሄፐታይቲስ B ልጅዎ በህይወት ዘመኑ ሁሉ ሊሸከመው የሚችለው ከባድ ህመም ነው። ነፍሰ ጡር ከሆኑ እና ሄፐታይቲስ B ካለብዎት፣ ቫይረሱ በወሊድ ጊዜ በደም ንክኪ አማካኝነት አዲስ የተወለደ ልጅዎን ሊበክል ይችላል። ልጅዎን ከኢንፌክሽን ለመከላከል እና የራስዎን ጤና ለመጠበቅ፣ በእርግዝናዎ ወቅት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን በጊዜ አግኝተው ስለ ሄፐታይቲስ B ያነጋግሯቸው።

**በእርግዝና ወቅት እና ከዚያ በኋላ የራስዎን እና የልጅዎን እንክብካቤ ለመከታተል ይህን ካርታ ይጠቀሙ!**

## ለእናት

### በእርግዝና ወቅት

- ✓ የሄፐታይቲስ B ደረጃዎን እና የጉበት ሁኔታዎን ለማወቅ በእርግዝናዎ ወቅት ቀደም ብለው የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ለሄፐታይቲስ B እንክብካቤ ያግኙ።
  - አስፈላጊ ከሆነ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የሄፐታይቲስ B መድሃኒቶችን ማዘዝ ይችላል።

### በወሊድ ጊዜ

- ✓ ሆስፒታል ውስጥ ያሉ ሰራተኞች እርስዎ ሄፐታይቲስ B እንዳለብዎት ማወቃቸውን ያረጋግጡ።
- ✓ ልጅዎን የሚንከባከበው የጤና እንክብካቤ አቅራቢ እርስዎ ሄፐታይቲስ B እንዳለብዎት ማወቁን ያረጋግጡ።

### ከወሊድ በኋላ እና ቀጥሎ ባሉት ጊዜያት

- ✓ ከ 1- 2 ወራት፣ ለሄፐታይቲስ B እንክብካቤ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይከታተሉ።
  - ይህ በተለይ በእርግዝና ወቅት ህክምና ጀምረው ከነበር አስፈላጊ ነው።
- ✓ ቢያንስ በየ 6 ወሩ ለሄፐታይቲስ B ቁጥጥር የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይከታተሉ።

**በእርግዝና ወቅት የትዳር አጋርዎ እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ መመርመራቸውን እና የሄፓታይቲስ B ክትባት መውሰዳቸውን እርግጠኛ ይሁኑ።**

## ለልጅ

### በወሊድ ጊዜ

ከኢንፌክሽን ለመከላከል ልጁ በተወለደ በ 12 ሰዓታት ውስጥ 2 ክትባቶች መውሰድ አለበት፦

- ✓ አንድ የሄፓታይቲስ B ኢሚዩን ግሎቡሊን (HBIG) ክትባትፐ
- ✓ የሄፐታይቲስ B ክትባት 1ኛ ክትባት

### 1-2 ወራት

- ✓ ልጅዎ ለ 2ኛ የሄፐታይቲስ B ክትባት ጊዜው ደርሷል።

### 6 ወራት

- ✓ ልጅዎ ለ 3ኛ የሄፐታይቲስ B ክትባት ጊዜው ደርሷል።

### 9-12 ወራት

- ✓ የሄፐታይቲስ B ሁኔታውን ለማወቅ እና የጥበቃ ደረጃውን ለመመዘን ልጅዎ የደም ምርመራ ያስፈልገዋል።

### ጡት ማጥባት፦

- ✓ ልጅዎ ከእርስዎ ደም ጋር የሚኖረውን ንክኪ ለመቀነስ ስለ የጡር ማጥባት ድጋፍ እና እንዴት የተሰነጠቀ ወይም የሚደማ የጡት ጫፍን መከላከል ወይም መቆጣጠር እንደሚችሉ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።
- ✓ በወሊድ ጊዜ አዲሱ ህጻን የሄፐታይቲስ B ክትባት እና የሄፓታይቲስ B ኢሚዩን ግሎቡሊን ከወሰደ፣ በጡት ማጥባት በኩል የሄፐታይቲስ B ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ዕድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ልጅዎ አንድ ጊዜ እነዚህን ክትባቶች ከወሰደ በኋላ፣ ጡት ማጥባት አስተማማኝ ነው።

Washington State Department of Health

doh.wa.gov/hepbhub

DOH 420-441 October 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የሚከብዳቸው ደንበኞች፣ እባክዎ በ 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ። ከ North East Medical Services የተወሰደ፣ www.nems.org።